PDF-XChange
Click to buy NOW!
www.docu-track.com

ጀግንነታችን የት አለ?

የተከበራችሁ ወገኖቼ ይህን ጽሁፍ ለአንባቢያን ሳቀርብ ውንጀላው እኔንም ጨምሮ በመሆኑ ወነጀልከን በሚል ቅር እንዳትሰኙብኝ አደራ እላለሁ፡ እውነቱ ግን ምን እንደሆነ ለማየት መሞከር አለብን፡፡

“ ለጣሊያን የተገዛህ ውጉዝ ሁን” ብለው ስላሉ አቡነ ጴጥሮስ ፍርድ ቤት ቀርበው በብላታ አየለ ገብሬና በነጋድራስ ወዳጆ አሊ በመሀል ዳኛው ኮንቴ ዴ ላ ፖርቶ አቀነባባሪነት በአንድ ድምጽ የሞት ፍርድ ተፈረደባቸው፤ ውሳኔው ቀደም ብሎ ተካሂዷል ነገር ግን ፍትህ ያለ ለማስመሰል ጉዳዩ ፍርድ ቤት ቀርቧል፤(የ 20ኛው ክፍለዘመን ኢትዮጵያ በጥላሁን ብርሃነ ስላሴ ገጽ 213) ሕዝባቸውን ነጻ ለማውጣት የሕይወት መስዋዕትነት ሲያደርጉ መርሆአቸውን ሊከተሉ የሚገባ ካህናት የሰጡት መልስ ከዚህ የሚከተለው ነበር፤

ሚያዝያ 27 ቀን 1928 ዓ.ም. ንጉሠ ነገሥቱ በሄዱ በሶስተኛው ቀን የጣልያን ወታደር በአዛዡ ጄኔራል ባዶሊዮ እየተመራ በየካ በኩል ሲገባ የኦሮቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ካህናት ልብሰ ተክህኖ ለብሰው በመሰለፍ ልክ ጄኔራል ዲ ቦኖ አድዋ ሲገባ እንዳደረጉት ለጄኔራል ባዲሊዮም የክብር አቀባበል አደረጉለት፤፤(የ20ኛው ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ በጥላሁን ብርሃነ ስላሴ ገጽ 190) የዛሬዎቹም የቤተክህነት ኃላፊዎች ከመንግስት ጋር እጅና ጓንት በመሆን በወገናቸው ላይ ግፍ ሲፈጽሙ በየእለቱ የምንታዘበው ነው፤፤

በላይ ዘለቀ ጣልያንን መውጫ መግቢያ አሳጠቶ ሲያስጨንቅ በኖረ የንጉሱን ሥልጣን አላከበረም በሚል እንዲሰቀል ሲያዙ በላይ ዘለቀ ለአገራቸው ያደረጉትን ተጋድሎ  ንጉሱ ጠንቅቀው ያውቁ ነበር፤ (ለቀዳሚ መላክተኛቸው ለአዛዥ ከበደ ተሰማ በላኩት ደብዳቤ ተራ ቁ.11 ላይ በልጅ በላይ ዘለቀ በኩል ከጠላት ነጻ የሆነ መንገድ እንዳለ ይጠቁማሉ የታሪክ ማስታወሻ ከደጃዝማች ከበደ ተሰማ ገጽ 214 ከግርማዊ ጃንሆይ የተላከውንም መልክት ተቀብለው ከራስ ኃይሉ በለው (ባንዳ) ጋር የነበራቸውንም ጠብ ወደ ጎን አድርገው በኢትዮጵያ ባንዲራ ስር ሆነው ለኢትዮጵያ ነጻነት እንደሚታገሉም ቃል የገቡበት መረጃም ነበራቸው ገጽ 265) እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ ራሳቸውን ደጃዝማች ብለው የሾሙት በላይ ዘለቀ ከኃይሉ ማሞ ጋር በተቀነባበረ ወንጀል ተከሰው ሁለቱም ሕዝብ በተሰበሰበበት እንዲገደሉ ሲደረግ ውለታቸውን የሚያውቀው ሕዝባቸው እኚህ ታላቅ ሰው እንዲድኑ ያደረገው ነገር የለም፡፡

በታህሳስ ወር 1953 የክቡር ዘበኛ አዛዥ የነበሩት ብርጋዴር ጀኔራል መንግስቱ ንዋይ ከወንድማቸው ከግርማሜ ንዋይ ጋር ሆነው የመንግስት ግልበጣ ሙከራ ያደረጉት የተበደለውን ሕዝባቸውን ነጻ ለማውጣት እንጂ የግል ሕይወታቸውን ለማሻሻል አልነበረም፤ ነገር ግን መንግሥቱ ንዋይ አዲስ አበባ ሲሰቀሉ የሞቱለት ሕዝብ እሳቸውን ለማዳንም ሆነ ትግላቸውን ለመቀጠል ያደረገላቸው ነገር አልነበረም በየቤቱ እርስ በርስ ከማውራት በስተቀር፡ ይህ ማለት ግን የነዚህ የተጠቀሱ ሰዎች መስዋዕትነት ምንም ለውጥ አላመጣም ማለት አይደለም የንጉሱ ኃይል ፍጹማዊ አለመሆኑን በማሳየቱ ሰራዊቱን በድጋሚ እንዲነሳሳ የራሱ የሆነ አስተዋጽዖ አድርጓል፡፡ ዛሬ በወያኔ ታስረው በይስሙላ ፍርድ ቤት የሚመላለሱትን መሪዎች ስናስብ የብርጋዴር ጀኔራል መንግስቱን የመጨረሻ ንግግር እንድናስታውስ ይጋብዘናል ልጠቅስ እፈልጋለሁ “ የፍርድ ወንበር ላይ ከመቀመጣችሁ በፊት በእኔ ላይ የምትሰጡትን ፍርድ  ታውቁት እንደነበር ሳስበውና ፍርድ እስከዚህ መድረሱን ስታዘብ ሃዘኔ ይበዛል“ ከይሁን ዓለም ሰገድ ፋና ወጊ ገጽ 105፡፡ ዛሬ ከ 46 ዓመት በኋላ ዳኞቻችን በአቶ መለስ ትዕዛዝ የሙያቸውን ሥነ ምግባር (ethics) ያልተከተለ ፍርድ ሲያካሄዱ ስናይ ምን ያህል ለግል ጥቅም ፍራቻ እንደተገዙ ከማሳየቱም በላይ ባሳለፍናቸው ዓመታቶች ጉዞአችን የኋሊት እንደነበርም ይጠቁመናል፡፡ “ዋ! ዋ! ለናንተና ለገዢአችሁ

PDF-XChange Click to buy NOW! www.docu-track.com

PDF-XChange Click to buy NOW! www.docu-track.com

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃሳቤ በዝርዝር ገብቶት በአንድነት በሚነሳበት ጊዜ የሚደርስባችሁ መዓት የሚያሰቅቅ ይሆናል መጋቢት 19 ቀን 1953 ዓ.ም." ይህ የመንግሥቱ ንዋይ ትንቢት ለዛሬስ አይሆንምን? (ኢያሱ በኃይለ ሥላሴ፣ ኃይለሥላሴ በመንግሡቱ ኃይለማርያም፣ መንግሥቱ ኃይለማርያም በመለስ ዜናዊ በአሰቃቂ ሁኔታ የአስተዳደር ዘመናቸው እንደተፈጸመ ሁሉ የመለስ ዜናዊም ማክተሚያ ካለፉት መሪዎች የተለየ እንደማይሆን ለመገመት አያዳግትም)

በ 1966 የፈነዳው አብዮት  ያለምንም ደም እንከኗ ይውደም ብሎ ተነስቶ ሥልጣኑን በተቆናጠጠ ማግስት ባገሪቱ ሃብት የተማሩትንና ለኢትዮጵያ ትልቅ ውለታ የዋሉላትን ዜጎቿን ያለምንም ፍርድ በጅምላ በ 60ዎቹ ሚኒስትሮችና ባለሥልጣናት ጀምሮ ሲጨፈጭፍ ከርሞ፡ፈሪና የማንተባበር መሆናችንን ሲያይ በቀይ ሽብር ስም ለተጨፈጨፉት ጭራሽ የጥይት ዋጋ ሁሉ ማስከፈል ጀመረ (ወያኔም ከአምሳያው ከደርግ ባገኘው ትምህርት ወገኖቻችንን ያለፍርድ ለገደለበት የጥይት ዋጋ ከማስከፈሉም ሌላ የገደሉብኝም ተቃዋሚዎች ናቸው ብላችሁ ፈርሙ አለበለዚያ ሬሳው አይሰጥም የሚል ፈሊጥ አመጣ) ፤ወንድሞቻችንን እህቶቻችንን ልጆቻችንን ሬሳ ፊት ቆመን ጸረ አብዮተኞች ናቸው መፈክር አርጉ አታልቅሱ ስንባል ትዕዛዝ ሰናከብር ከረምን ይሄ ፈሪነት ካልሆነ ሌላ ምንድን ነው? ብዙዎቻችን በቤታችን በራሳችን ካልመጣ አንነቃም ባሕላችን ነግ በኔ ብሎ የሚያስተምረንን እንዘነጋለን፡ ለግል ጥቅም መሬት፣ቤት፣ንዋይና ሥልጣን የመሳሰሉት ጥቅማ ጥቅሞች ከአገራችን ከወገናችን በላይ ሆነው እናገኛቸዋለን፡ ይህ ደግሞ እየረገጡን ዕያዋረዱን ለሚኖሩት መሪዎቻችን ሲሳይ መሆን ነው።

የመንግሥቱ ንዋይ ፍርድ ሲገርመን ተመሳሳይ ሁኔታ በደርግም አጋጥሞናል፤ በመንግሥቱ ኃይለማርያም ላይ የግልበጣ ሙከራ ተደርጎ ግንቦት 1989 ሲከሽፍ መንግሥቱ ሰዎቹን (ጄንራሎቹን) ከመረሸኑ በፊት ሕጋዊ ፍርድ የሰጠ ለማስመሰል ጋዜጠኞች ባሉበት የውጭ ታዛቢዎች ባሉበት ወንጀለኛ የተባሉት ተከሳሾች በጄኔራል ተስፋዬ በሚመራው ወታደራዊ ፍርድ ቤት ተልከው ነበር፤ከጄኔራል ፋንታ በቀር የተቀሩት በሙሉ ፍርድ ቤት ተገኝተዋል፡ የፍርድ ቤቱ ሁኔታ መንግሥቱን ስላላስደሰተው በሌላ አነጋገር የሚፈልገውን ውሳኔ ሊያመጣ አይችልም ብሎ ስለገመተ ያለ ምክንያት ጄኔራል ተስፋዬ ገ/ኪዳንን ከበላይ ዳኝነት ሽሮ በምትካቸው ጄኔራል አስራት ብሩ ተሾሙ፤ ሥልጣን በጸደቀ በማግሥቱ ጄኔራል አበራ በ 11 ጄኔራሎች ላይ የሞት ቅጣት ለባሕር ኃይል አዛዡና ለሌሎችም ጽኑ እስራት እንዲበይኑ ከመንግሥቱ በደረሳቸው መሰረት ውሳኔው ተካሄደ ( The Rape of a nation by Yehwalashet Girma page150) ከወያኔ ፍርድ ቤቶችና የዳኞች ብይን ጋር ተመሳሳይነቱ ምንም የሚያጠራጥር አይደለም።

የደርግ ሲገርመን ሲያንገበግበን ጭራሽ አንድነታችንን የሚያናጋና የማይቀበል አባቶቻችን ቅድም አያቶቻችን በደማቸው አስከብረው ያቆዩንን ባንዲራችንን ጨርቅ ነው የሚል በጎሳና በሃይማኖት አንድነታችንን የሚበታትን ወያኔ የሚባል ፀረ ኢትዮጵያ የሆነ መንግስት በምዕራባውያን ዕርዳታ ቂጢጥ ብሎ ሲፈጀን ሲያፋጀን ጉድ እያልን አሁንም እናያለን። እንደነ ዶ/ር ሀብተማረርያም አሰፋ የመሳሰሉ የወያኔ ምሁሮች አዲስ ታሪክ ሊጽፉልን ይሞክራሉ ከተማረ የማይጠበቅ ጥላቻ ላይ የተመሰረተ ታሪክ ለትውልድ ያስቀራሉ (የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባህሎች)

በሰላማዊ መንገድ ታግለው ነጻ ሊያወጡን የተነሱት መሪዎቻችን፣ ሆ ብለን መርጠናቸው ዛሬ በእስር ቤት ሲማቅቁ ልንረሳቸው አይገባም፣ ውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ በዚህ አጋጣሚ ለራሱ ስልጣን ሲሯሯጥ፤ የግል ጥቅሙን ለማስከበር ወገኑን ሲያጋልጥ ማየት አሳዛኝና አሳፋሪም ነው፡  መብታችንን ለማስከበር ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተው በጠራራ ጸሃይ የተደፉትን ወገኖቻችንን ልንዘነጋቸው አይገባም፤ ደማቸው ደመ ከልብ ሆኖ ሊቀር አይገባም

አገር ውስጥ ያለው ሕዝባችንም ሆነ ውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ ታምር ተፈጠሮ ነጻ አውጪ ነጻ እስከሚያወጣው የሚጠብቅ ነው፡ እስከ መቼ ነው የምንጠብቀው? ለምንድን ነው በሚሊዮን የሚቆጠረውን ሕዝብ ነጻ ለማውጣት ጥቂቶች የሚሞቱት፣ የሚታሰሩት፣ የሚሰቃዩት የባህር በራችን ተገንጥሎ ተሰጥቶ፣ ኢኮኖሚያችን በጥቂት ዘረኞች እጅ ሆኖ፣ የመናገር፣የመጻፍ፣ የመሰብሰብ፣ መሪዎቻችንን የመምረጥ መብት ተነፍጎ፡ ከዚህ በላይ ምን እስኪሆን ማ መጥቶ ነጻ እስኪያወጣን ይጠበቃል ኅበዝ እንበራታ አንድነት ኃይል ነው።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኖራለች

ታዛቢው ከሆላንድ (ካበደ)
የካቲት 24/1999